# አቢቹ

*ወቅቱ 1929 ዓ.ም ነበር። ፋሽት ጣልያን ኢትየጵያ ሀገራችንን ወሮ እያለ ኢትዮጵያውያን ቋንቋ እና ጎሣ ሳይለያያቸው ውድ የጋራ አገራቸውን ነፃነት ከጥቃት ተከላክለው ለመጠበቅ ያደርጉት የነበረውን መሥዋዕትነት ቁንጥሮ የሚያሳይ፣ የቼክ ተወላጅ ኢንጂነር አዶልፍ ፓርለሳክ በወቅቱ በጦር አማካሪነት አገራችንን ሲያገለግል በነበረበት ወቅት በመስክ ላይ እንዳለ የጻፋቸውን ማስታወሻዎች አጠናቅሮ ተጫነ ጀምበሬ መኮንን በአማርኛ ከተረጎመው የ "የሐበሻ ጀብዱ" ከተባለው መጽሐፍ በቀጥታ የተወሰደ ነው። (ተፈራ ድንበሩ)*

"ደጃዝማች፣ ምን ተፈጠረ?" ብዬ ጠየቅኩት። "ትናንት በጦርነቱ ሁለት ፊተውራራዎች አጣሁ" አለ፤ ማዘን ሳይሆን ፍጹም ቆጣ ብሎ። "ብዙ ወታደሮች አጣህ እንዴ?" ሲል ኮሎኔል ላቀረበለት ጥያቄ፣ "አሁንም ከ20 ሺ በላይ ጦር አለኝ"" ችግሩ ግን የወረጃርሶው ቀዳሚ ጦር ሁለቱን ፊታውራሪዎች ማለት መሪዎቼን አጣብኝ" አለና አሰብ አደርጎ፣ "አሁን የነዚህ ሹሞች ጥያቄ" ብሎ ሊነግረን የፈለገውን የሹሞቹን ነገር መልሶ ትቶ አሽከርዬው ሹሞቹን እንድያስገባ አዘዘው። በዚህ ጊዜ ደጃዝማች ከሹሞቹ ጋር ብቻውን ያወራ ዘንድ ልንወጣ ብድግ ስንል "ቁጭ በሉ" አለን፤ አሁን ቃሉ ትዕዛዝ የተሞላበት ነበር።

ወዲያው ሳቅ ብሎ በይቅርታ ዓይን እያየን፣ "ምክራችሁን እፈልጋለሁ" አለን። ሹሞቹ ወደ ድንኳኗ ገብተው በአንድ ላይ ለደጃዝማቹ የሚገባውን የክብር ሰላምታ ካቀረቡ በኋላ ለጥቂት ጊዜ እርስ በርሳቸው ተያዩና አንድ በእድሜያቸው ጠና ያሉ ሹም በኦሮምኛ አጠር ያለ ንግግር አደረጉ። ቀጥለውም ሌሎች ሹሞች አንዱ በአማርኛ ሌላው በኦሮምኛ ለደጃዝማቹ ችግራቸውን አስረዱ።ሁሉም ሹሞች ያወሩት ስለተመሳሳይ ችግር ነበር።

ሹሞቹ ችግራቸውን አስረድተው ንግግራቸውን ጨርሰው እንደቆሙ፣ ደጃዝማች አበራ ወደኛ ዞር ብሎ የሹሞቹን አቤቱታ በጥቂቱ ካስረዳን በኋላ የኛን መልስ ሳይጠብቅ ቆመው ወደሚጠብቁት ሹሞቹ ፊቱን መልሶ ወሳኔውን ማምሻው ላይ እንደሚያስውቃቸው ነግሯቸው አሰናበታቸው።

ሹሞቹ ተሰናብተው እንደወጡ ደጃዝማች ትንሽ ሲያስብ ቆይቶ ድንገት ብደግ ብሎ ከድንኳኗ ወጣ። እኛም በደመነፍስ ተከተልነው። እንደምንከተለው የገመተ መሰለኝ ፊቱን ሳይመልስ እርምጃችንን ጨምረን እንድንከተለው ነገረን። ከደጃዝማቹ ፈጣን እርምጃ እኩል መሄድ ባለመቻላችን እሱ ጋ ለመድረስ እንደመሮጥም እየቃጣን ትንሽ እንደተጓዝን፣ ደጃዝማቹ አንድ የተጠረበች የምትመስል ጥቁር ድንጋይ አጠገብ ሲደርስ ፈጣን እርምጃውን ገትቶ ቆም ብሎ ጠበቀን። ከድንጋይ ላይም እንድቀመጥ ጋበዘንና እሱም ከመሀላችን ተቀመጠ።

ድንጋይዋ ላይ እንደተቀመጥን፣ “ያችን ዋርካ ታይዋታላችሁ?” አለን። ሁለታችንም በአንድ ጊዜ አዎ” ብለን መለስን። ደጃዝማች አበራ አሁንም ወደ ዋርካዋ ፍዝዝ ብሎ እየተመለከተ፣ “ሌላስ ምን ይታያችኋል?” ሲል ጠየቀን። እኔ ይታየኝ የነበረውን ስናገር ኮሎኔል “ከዋርካዋ አጠገብ አነስ ያለች ቋጥኝ አለች። በቋጥኟ ላይ አንድ ሰው የተቀመጠ ይመስላል” ሲል ግልጽ አድርጎ አስረዳው። “በትክክል” አለና ደጃዝማች በመቀጠል “የኔም ችግር በዚያች ቋጥኝ ላይ የተቀመጠው ሰው ነው” አለን። “እንዴት ማለት? አልገባኝም?” አለ ኮለኔል ኮኖቫሎቭ። ለነገሩ የደጀዝማቹ ችግር እኔንም ሊገባኝ አልቻለም።

ደጃዝማች አበራ ጥቂት ተከዝ ብሎ እንደማሰብ ካለ በኋላ “ትናንት ሁለት የጦር መሪ ፊታውራሪዎች እንዳጣሁ ነግሬያችኋለሁ አይደል?” ብሎ ጠይቆ መልስ ሳይጠብቅ በመቀጠል፣ “እነዚያ ፊታውራሪዎች የወረጃርሶው ቀዳሚ ጦር መሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ወንድማማቾች ነበሩ” አለና አሁንም ፍዝዝ ብሎ በዚያች ቋጥኝ ላይ ተኮማትሮ የተቀመጠውን ሰው እያየ “ታዲያ የሹሞቼ አቤቱታ ሁነኛ ሰው መርጬ እንድሾምላቸውና አሁንም ግንባር ቀደም ሆነው በመዋጋት የመሪዎቻቸውን ደም ይከፍሉ ዘንድ ነው” አለ፤ አሁንም ዓይኑን ከዚያች ቋጥኝ ላይ ሳይነቅል።

“ታዲየ ችግሩ ምንድነው? ማለቴ አንዱን ጎበዝ ተዋጊ መርጠህ አትሾምላቸውም እንዴ?” ሲል ኮሎኔል አከታትሎ ጠየቀው። አሁንም ዓይኑን ከቋጥኟ ላይ ሳይነቅል፤ “ኮሎኔል፤ ነገሩ እንደምትገምተው ቀላል አደልም” አለና በመቀጠል “ለነገሩ ጃርሶዎች አሁንም አንድ ፊታውራሪ አላቸው”፤ አለ ሳቅ እንደማለት ብሎ።

“ታዲያ ወረጃርሶዎች ፊታውራሪ መሪ ካላቸው ስለምን ሌላ መሪ እንድትሾምላቸው ይጠይቁሃል?” ስል እንዲያብራራልኝ አስቤ ጠየቅኩት። አሁን ፊቱን ወደኛ መልሶ ሳቅ አለና እንደገና ፊቱን ወደ ቋጥኟ መልሶ፣ “ይታያችኋል ያ ሰው? ቋጥኟ ላይ የተቀመጠው?” አለን በድጋሚ። አሁንም በአንድነት “አዎን” አልነው። “ቋጥኟ ላይ የተቀመጠው ሰው የመጨረሻው የወረጃርሶ ፊታውራሪ...” አለን።”እውነቱን ለመናገር የችግሩ መሠረት አልገባኝም? ጃርሶዎች ፊታውራሪ ካላቸው ለምን አዲስ  ፊታውራሪ ይጠይቁሃል?” አልኩት።

አሁንም በመጠኑ ፈገግ ብሎ፣ “አንደኛ ይኼ ፊታውራሪ ሲበዛ 16 ወይም 17 ዓመት ቢሆነው ነው። ሁለተኛ ትናንት አንዱን ወንድሙን ከጦር ሜዳ አስመጥቶ ዋርካዋ ሥር ቀብሮ አነሆ ከቋጥኟ ላይ ሳይነሳ ሁለተኛ ቀኑን ይዟል። ሦስተኛ ሹሞቹ በዚህ መልኩ ከቀጠለ እንደ ወንድሞቹ ጥሩ መሪ አይደለምና ጥሩ ተዋጊ አዋጊ ይሾምልን ባዮች ናቸው። አሁንስ ገባህ?” ሲል በፌዝ አይነት ነገር ጠየቀኝ። በመቀጠልም “የኔ ችግር ግን እሱ አይደለም አለን፤ አሁን እዝን እና ጭንቅ ብሎ። “አየህ ጌታው፣ እውነቱን ለመናገር እኔ በጃርሶው ጦር ላይ ምንም ኃይል የለኝም። ጦሩ ታማኝነቱ ለሁለቱ ፊታውራሪዎች ብቻ ነበር። ይኼን አስከ አራት ሺ ድረስ የሚቆጠረውን ሠራዊት አንዱን ቀኛዝማች ወይም ፊታውራሪ አድርጌ ብሾምለት ለምሾመው ፊታውራሪ ላይታዘዝ ይችላል። እና ያለኝ አማራጭ የመጨረሻውን ፊታውራሪ ሐዘኑን ጨርሶ እንደ ወንድሞቹ ሁሉ ጦሩን እንዲመራ

ማሳመን ወይም አንዱን ሽሜ ቀዳሚው የጃርሶ ጦር ፍርክስክሱ ሲወጣ ማየት ብቻ ነው" አለን።

"አይ ሌላ ዘዴ ይፈለግለታል፣ ለማንኛውም ለውሳኔ አትቸኩል" አለው ኮሎኔል ኮኖቫሎቭ።

"አይ ኮሎኔል እየሰማህ! ዛሬ ማምሻው ላይ ቆርጬ ውሳኔዬን ለሹሞቹ መንገር አለብኝ" አለው አሁን ሳቅ ብሎ፣ "አለበለዚያማ ጥሬ ሥጋዬን በቁሜ ይበሉታል" አለና በሳቅ ተንፈራፈረ።

"አያችሁ ገና ከሰላሌ ሳንነሳ የጃርሶው ጦር መሪ ፊታውራሪ በድንገት ታመው ሞቱ። ከዚያ ሁለቱ ወንድማማቾች ጦራቸውን በጥንድ በሕብረት እየመሩ የመጨረሻውን ወንድማቸውን አቢን አስከትለው መጡ። ትናንት አንዱ በጦር ሜዳ በጀግንነት ጦሩን እየመራ ግንባር ቀድሞ ሲዋጋ እንደጀግና በደብረ አምባ ወደቀ። ሁለተኛው ፊታውራሪ ይማረክ፣ በመድፍ ጥይት ብትንትኑ ወጥቶ ይውደቅ አይታውቅም። አሁን የቀረኝ ገና የ16 ዓመት ልጅ፣ ገና አባይን ሳንሻገር እናታቸው መጥተው አደራ ያሉኝን ልጅ ምን ላድርገው? ጦር ሰጥቼው ወደ ሰላሌ ብልከው እንኳ ከትግራይ ሽፍቶች ቢያመልጥ ከራያዎች ወጥመድ አያልፍም። ጦሩን እንዲመራ ገፋፍቼ እንደ ወንድሞቹ ቢወድቅና የፈጣሪ ሥራ ሆኖ ሰላሌ ብመለስ እንዴት አድርጌ የአሮጊቷን ዓይን ማየት እችላለሁ? በዚህ ፈጣሪ ብቻ ይርዳኝ" አለ ደጃዝማች አበራ።

በኋላ ላይ ስለ አቢ እንደሰማሁት አባትዬው ሁሌም ትንሹ ልጃቸው ዘመናዊ ትምህርት ተምሮ ዘመናዊ ሰው ሆኖ ከጊዜው ጋር እንዲራመድላቸውና እንደሳቸው ከመሬት ጋር ተጣብቆ እንዳይቀር በማለት፣ ከልጅነቱ ጀምረው አዲስ አበባ በመላክ አስተምረውት እነሆ በሚቀጥለው ዓመት ወደ ፈረንሳይ ሀገር ለከፍተኛ ትምህርት ተጓዥ ነበር። ምን ያደርጋል፣ ሀገር ተወረረችና ትምህርቱም ቀርቶ ሁሉም ወደ ጦር ግንባር ተባለና አቢቹም አባቱን በጃርሶ ቀብሮ፣ እናቱን ብቻቸውን ጥሎ፣ ሁለት ወንድሞቹን ተከትሎ፣ በደጃዝማች አበራ ጦር ሥር ተሰልፎ፥ ተንቤን ደርሶ፣ በመጀመሪያው ቀን ውጊያ ሁለት ወንድሞቹንና የጦር አለቆቹን አጥቶ፣ የአንዱን ወንድሙን ሬሳ በዋርካዋ ሥር ቀብሮ፣ ሁለተኛውን በመንፈሱ እየፈለገና እየተሰናበተ እነሆ እዚቹ ቋጥኝ ላይ ሲቀመጥ ሁለተኛ ቀኑ ነው።

አቢቹ እንደባላገሮች ሹሞች የሚያስብ ሰው አይደለም። የተማረና ያለዕድሜው የበሰለ የልጅ አዋቂ ቢሆንም ገና ከጅምሩ እግዚአብሔሩ መከራውንና ሐዘኑን ጭኖበት፣ በልጅ አዕምሮው ሌት ተቀን እያሰበ መወሰን ተቸግሮ ተቀምጧል። እንዲህ ሁላችንም ስለ አቢቹ እየተጨነቅንና ለደጃዝማቹ ጭንቀት መፍትሔ እየፈለግን ዝም እንዳልን ኮሎኔል ኮኖቫሎቭ "እድልና ጊዜ ስጠው። ምንም ወጣት ቢሆን ዞሮ ዞሮ መወሰኑ አይቀርም። ምናልባትም እንዲህ የማሲንቆ ጨዋታ፣ ለቅሶና ዋይታ በሰፈሩ ከልክሎ፣ ብቻውን በቋጥኟ ሥር ተቀምጦ በራሱ መንገድ ወንድሞቹን እየተሰናበተና የራሱንም የወደፊት እጣ እየወሰነ ይሆናል" ብሎ አጽናናን።

እኔም የኮሎኔልን ንግግር እያዳመጥኩ አቢቹን የማናገር ስሜቴ እየገፋ መጥቶ ምክንያት ፈልጌ ከደጃዝማች አበራና ከኮሎኔል ጋር ተሰናብቼ የምሄድበትን ጊዜ ስጠብቅ፣ ከሩቅ የኛን አንበሳ የሆነ ነገር የዞ ወደ አቢቹ ሲያመራ አየሁት። አንበሳ ከያዘው ነገር በዋንጫ ለአቢቹ ከቀዳና ከሰጠው በኋላ ወረድ ብሎ ከአቢቹ እግር ሥር ተቀመጠ። እኔም አንበሳ ሲመለስ ወሬ ለመቃረም ወሰንኩና ሀሳቤን ቀይሬ ከደጃዝማችና ከኮሎኔል ጋር ወደ ሰፈር ተመለስኩ።

አንበሳ ወደ ሰፈር ተመልሶ ገና ወደ ድንኳኗ ከመግባቱ በጥያቄ አጣደፍኩት። አንበሳ በተረጋጋ መንፈስ ብዙ በጣም ብዙ ነገር ስለ አቢቹ ካወራኝ በኋላ፣ በመቀጠል የአቢቹ አባት ከመሞታቸው በፊት ለአቢቹ የመረጡለትን እጮኛ ውበትና ቁንጅና እያሞጋገሰ አወራልኝ። በመጨረሻም እኔ በጉጉት እጠብቅ የነበረውን ወሬ አነሣና እንደ አቢቹ እምነት ትልቁ ወንድሙ ያልሞተና በጣልያኖች ምርኮ ወድቆ እንደሚሰቃይ፣ ወንድሙን ነፃ ለማውጣት መውሰኑንና ሌሎችም ሌሎችም ብዙ ብዙ ነገሮችን አጫወተኝ። እኔም አንበሳዬን አመስግኜ የቋጠርኳትን ወሬ ይዤ ወደ ደጃዝማች አበራ ድንኳን ተፈተለኩ።

ይሁን እንጂ እኔ ይዤው የመጣሁትን ወሬ ሳልተነፍስ የደጃዝማቹ አሽከር መጥቶ አፉን በሸማ ሸፍኖ፣ አቢቹ ከደጃዝማቹ ፊት ይቀርብ ዘንድ እንደሚጠይቅ ሲነግረን፣ ደጃዝማች አበራ በስሜት ከተቀመጠበት ተነሥቶ ግባ በለው አለ። አቢቹ ገና ከደጃዝማቹ ድንኳን በራፍ አለፍ እንዳለ ከደጃዝማቹ እግር ሥር ወድቆ ለደጃዝማቹ የሚገባውን የክብር ሰላምታ ለማቅረብ ወረድ ሲል ደጃዝማች አበራ አፈፍ አድርጎ አንሥቶ አቀፈው። ሁለቱ ወጣቶች ለረጅም ጊዜ ተቃቅፈው ከቆዩና ደጃዝማች የአቢቹን ትከሻ መታ መታ እያደረገ ካረጋጋው በኋላ “እሺ አቢቹ፣ ታደያ ምን አሰብክ? አለው።

አቢቹ ብዙም ሳይጨነቅ አጠር አድርጎ ወንድሙን ነፃ ለማውጣት የጦር ሰፈሩን ንጋት ላይ ለቅቆ ከጥቂት ወታደሮቹ ጋር እንደሚሄድና፣ የጃርሶውን ጦር አጎቱ ቀኛዝማች ገለታና ቀኛዝማች ሼክ ሁሴን አባወርቂ በህብረት ይመሩት ዘንድ ደጃዝማቹን ተማጽኖና ተሰናብቶ ከመውጣቱ በፊት ሁላችንንም ወደ ሰፈሩ ጋብዞን ወደ ጦር ሰፈሩ ወረደ።

አቢቹ ጦር ሰፈሩ እንደደረሰ የራሱ የሆኑትን የመጨረሻ ንብረቱን ሦስት በሬዎች አረዳቸው። የኼን ያዩ ሌሎች የበታች ሹሞችም ቤት፣ የጦር ሜዳ ቤት፣ ያፈራውን ይዘው እየመጡ፣ የተከለከለው የማሲንቆ ጨዋታ ተፈቅዶ ሞቅ ሞቅ ሲል እኛም ግብዣውን አክብረን ተገኘን።

እንዲህ እኔ፣ ደጃዝማች አበራ፣ ኮሎኔል ኮኖቫሎቭና አቢቹ መደዳውን በበግ ቆዳ (ድብዳብ) ላይ ተቀምጠን እየበላንና አረቂና ጠጅ እየጠጣን ስንጫወት ቆይተን፣ አቢቹ ከተቀመጠበት ተነሥቶ ቆመና ሁሉም ፀጥ ሲል ጠብቆ የሚከተለውን አጠር ያለች ምስጋና የበዛባት ንግግር አደረገ።

> ስላከበራችሁኝና ስላጽናናችሁኝ እግዚአብሄር ያክብርልኝ፣ ታላቅ ወንድሜ ፋሽት ጣልያንን ሲዋጋ ሕይወቱ ብታልፍም የሱ ዓላማ ስላልሞተ ኢትዮጵያ አትሞትም፣

> የሱን የነፃነት አርማ አንስቼ ይኸው በመካከላችሁ አገኛለሁ፤ በወንድሞቼ፣ እህቶቼ፣ ዘመዶቼና ወገኖቼ ነፃነት አጥተው በባእድ እጅ ወድቀው፤ አገሬ በጠላት ተወራ ሙሉ ሕይወት አለኝ ማለት አልችልም፤ የኔ ወይም የጥቂቶቻችን ምቾት ያለ አገር ነፃነት እውነተኛ ምቾት ሳይሆን ለእርድ እንደሚዘጋጅ ከብት የመሰለ ሕይወት ስለሆነ ነፃነት አይባልም። ነፃነቱን የማያስከበር ደግሞ እንሰሳ ብቻ ነው እንጂ ሰው ሊባል አይችልም፤ ስለዚህ ወንድሜ ነፃ የሚሆነው ባገራችን ላይ የመጣው ጠላት ሲወገድ ብቻ ስለሆነ አገራችንን ነፃ ለማድረግ ቆርጬ ተነስቻለሁ፤ የሚመልሰኝ ምንም ኃይል የለም። የኔና አብረውኝ የሚዘምቱ ጓደኞቼ ውጤት ይዋል ይደር እንጂ በድል እንደሚጠናቀቅ ሙሉ ተስፋ አለኝ፤ እኔ ወይም ጥቂቶቻችን ብናልፍ የቀድሞ አባቶቻችን እያቶቻችን በደማቸው እንዳቆዩልን ወደፊትም አገራችን በደማችን ለልጅልጆቻችን ተከብራ እንደምተቆይ አምናለሁ።

ከዚያም ለአጭር ጊዜ ጥቂት ወታደሮች ይዞ ከጦር ሰፈር በመውጣት ወንድሙን ፍለጋ እንደሚሄድ፤ በሕይወት ካገኘው አገኘው፤ ሞቶም ከሆነ ከወንድሙ ጎን እንደሚቀብረው ተናገረ። ለጊዜው የጃርሶውን ጦር ቀኛዝማች ገለታና ቀኛዝማች ሼክ ሁሴን አባወርቁ እንዲመሩት ደጃዝማችን መማጸኑን፤ ሹሞቹ ለደጃዝማች አበራ ያላቸውን ታማኝነት በምኒልክ ስም እንዲምሉ ለምኖ ተቀመጠ። ጦሩም በሹሞቹ አመካኝነት እየተነሳ ለደጃዝማች አበራ ያለውን ታማኝነት በምኒልክ ስም እየተገዘተ፤ እየፎከረና እሽለለ ተቀመጠ።

ሌላው ከአቢቹ ጋር የአቢቹን ወንድም ነፃ ለማውጣት የሚሄዱት ወታደሮች የምርጫ ትእይንት ነበር። በመጀመሪያ ታላላቅ ሹማምንቶች እየተነሱ እየፎከሩና እየሸለሉ ከአቢቹ ጋር ለመሄድ ቆርጠው መነሳታቸውን ገለጡ። በዚህ መሀል አቢቹ ተነሥቶ ካመሰገነ በኋላ በመቀጠል አቢቹ የሚፈልገው ወደ 200 ገደማ ወዶ ገባ ጥሩ ተኳሽና ተዋጊ ጦር ብቻ እንደሆነ ገልጾ፤ አነዚህ 200 ተዋጊዎች ሚስቴን ጨርቄን ሳይሉ ፈጥነው መንቀሳቀስ የሚችሉ ወጣቶች ብቻ መሆን እንዳለባቸው ሲገልጽ በዚህ ንግግሩ በርካታ ሽማግሌ ሹማምንቶችን አስኮረፈ።

የሽማግሌ ሹሞችን ማኩረፍ ያዩት ብልሁ ቀኛዝማች ሼክ ሁሴን አባወርቁ  ተነሥተው "ልብ አድርጉማ ጎበዝ! መቼም እኔም ለጌታችን ከመሞትና ከመሰዋት በላይ ምንም ጽድቅ ነገር እንደሌለ አውቃለሁ። ከዚህ ውጪ አልመኝም። ከዚህስ በላይ የክብር ሞት ምን ይገኛል? ይሁን እንጂ እንደጉርምስና ጊዜዬ ከድንጋይ ድንጋይ እየዘለልኩ፤ እንደ ዝንጀሮ ገደል እየቧጠጥኩ ወጥቼና ወርጄ ፈጥኜ መዋጋት አይሆንልኝም፤ አርጅቻለሁ። እናም ለጌታችን እኔ ባይሆንልኝ የበኩር ልጄን ሰጥቻለሁ፡ ብለው ሲቀመጡ፣ ሌሎች ሹሞችም እየተነሱ ወጣት ልጆቻቸውን ለአቢቹ ሰጡ።

እነዚህ የሹሞች ልጆች ራሳቸው ከጦራቸው ወጣት፤ ደፋርና ጎበዞቹን እየመረጡ፤ ደጃዝማች አበራም አንድ ዘመዱን በታማኝነት አቢቹን ያገለግል ዘንድ ነግሮ ጥቂት ወታደሮች

ጨምሮ ሰጠው። ሊነጋጋ ሲል አቢቹ ወደ 200 ገደማ የሚሆኑ ወታደሮቹን እየመራ ከጦር ሰፈር ወጣ።

አቢቹ 200 ገደማ የሚሆኑትን ቀልጣፋ ወጣት ተዋጊዎቹን ይዞ በደጃዝማች አበራ ፊት ቀርቦ ተመረቀና በዚያው ሌሊት የጦር ሰፈሩን ለቅቆ ከሄደበት ሰዓት ጀምሮ አቢቹን አየሁ የሚል ሰው ጠፋ። ምንም እንኳ እኔም እንደሰው ሁሉ አቢቹን ከዚያን ምሽት ጀምሮ ባላየውም፣ ስለ አቢቹ ተጋነው የሚወሩ ጀብዱዎቹን በታላቅ ጉጉት እሰማ ነበር።

ይኼም ተጋኖ የሚወራው የአቢቹ ጀብዱ በራስ ካሣ የጦር ሰፈር በሰፊው ተሰራጭቶ በርካታ ወጣት ተዋጊዎች ዋናውን ጦራቸውን ትተው፣ ወርደው በዋናው የጦር ሜዳ የአርበኝነት ትግል ከጀመረው የአቢቹ ጦር ጋር መቀላቀል፣ መግባት ጀመሩ።

ምንም እንኳ ተማርኳል፣ የመድፍ ጥይት በጣጥሶ ጥሎታል፣ እና ሌላም ሌላም ወሬ ሲወራበት የነበረው የጃርሶው ፊተውራሪ ከደጃዝማች ወንደወሰን ጦር ጋር ወደ መልፋ ወርዶ ሲዋጋ ቆስሎ ሲያገግም ሰንብቶ፣ ከሳምንት በኋላ ወደ ዋናው የጦር ሰፈር ተመልሶ ጦሩን መምራት ጀመረ። ይሁንና አቢቹን መልሶ ከጦሩ ጋር እንዲቀላቀል ማድረግ ግን አልተቻለም ነበር።

ወንድምዬው ብዙ መልእክተኞች ቢልክም ግማሹ በዚያው ቀረ። የሚመለሱትም የአቢቹን ጦር ሲፈልጉ፣ ከሳምንት በላይ ሲንከራተቱ ሰንብተው ባዶ እጃቸውን ይመለሳሉ። በየቀኑ ዋናውን ጦራቸውን እየከዱ ወደ አቢቹ የሚኮበልሉተ ወጣት ተዋጊዎች ቁጥር ከቀን ወደ ቀን በመጨመሩና ይኼም ወሬ ከራሶች ድንኳን በመድረሱ እኔ፣ ኮሎኔልና ደጃዝማች አበራ ተጠርተን ከራሶቹ ፊት ቀረብን። ልጁንም ወደ እናት ጦሩ ይመለስ ዘንድ እንድናባብል ትእዛዝ ተሰጠን።

አቢቹ መጀመሪያ ላይ ከሰፈር እንደወጣ አነስተኛ የጣልያን የተበታተኑ ጦሮች እየፈለገ፣ በደረቅ ሌሊት አደጋ እየጣለ፣ ስንቅና ትጥቅ እየዘረፈ፣ ጦሩን ዘመናዊ መሣሪያ እያስታጠቀ፣ ማደራጀት ጀመረ። ከዚያ ጦሩን ይዞ የጠላት ጦር ባልጠበቀው ቦታና ሰዓት ድንገት እየደረሰ ያልተጠበቀና ያልታሰበ አደጋ እየጣለ፣ አልፎ አልፎም ሌሊት የጣልያኖቹን የጦር ሰፈር ሰብሮ እየገባ አደጋ እየጣለ፣ ንብረት እየዘረፈ፣ ከጦሩ የተረፈውን እና ጦሩ የማይፈልጋቸውን ነገሮች ወደ ዋናው ጦር መላክና ማከፋፈል ጀመረ።

እንዲህ ሳይታሰብ የሚጥለው አደጋ ጣልያኖቹን ክፉኛ ከመጉዳቱም በላይ የፋሽስቱን ጦር የበላይ አዛዦች ክፉኛ ስላስቆጣ፣ የጣልያን ወታደራዊ መኮንኖች ለትግራይ ሽፍቶች ከፍተኛ ገንዘብና ዘመናዊ መሣሪያ በመለገስ የትግራይ ሽፍቶች የአቢቹን ጦር አሳደው እንዲመቱ አደረጉ።

የትግራይ ሽፍቶች አቢቹን በመፈለግ ላይ እንዳሉ ጥር ወር መጨረሻ ቀትር ላይ ማርሻል ባዶሊዮ በቅርቡ ከሮማ ከተላኩለት ተኩስ ጦር ላይ ሁለት ሻለቃ ጦር ቀንሶ፣ ዘመናዊ

የሚባሉ መሣሪያዎችን አስታጥቆ፣ ወደ ተንቤን የላከው ጦር መንገድ ላይ ሲያዘግም አቢቹ ያያል። ከዚያም የጣልያኑን ሁለት ሻለቃ ጦር እንቅስቃሴ ከሩቅ ሆኖ ለረጅም ሰዓታት ሲከታተል ቆይቶ፣ ወታደሮቹን ይጠራና ጣልያኖቹ ምሽቱን ያሳልፉበታል ብሎ ወደ ገመተው ቦታ ቀድሞ በመሄድ፣ ሰሞኑን ከጣልያኖች ከዘረፋቸው በርካታ በቤንዚን ከተሞሉ ትላልቅ ቆርቆሮዎች ውስጥ አንድ አሥሩን ያህል በየቁጥቋጦው ውስጥ ያፈሱ ዘንድ ወታደሮቹን ያዝና፤ ከዚያ ራቅ ብሎ ይመሽጋል።

የአጋጣሚ ነገር ሊሆን ይችል ይሆናል። ጣልያኖቹ አቢቹ ሌሊቱን ያሳልፉበታል ብሎ በገመተው ቦታ ላይ ድንኳኖቻቸውን ተክለው ይሰፍራሉ። የአቢቹ ጦር እኩለ ሌሊት ላይ ያንን ቤንዚን የጠገበ ቁጥቋጦ እሳት ይለቅበትና በድንገት  የእሳቱ ወላፈን የቀሰቀሳቸው አዲሶቹ የጣልያን ወታደሮች መላው ጠፍቷቸው ሲደናበሩ፣ የአቢቹ ወታደሮች በእሳቱ ወጋገን እየተረዱ አዲሶቹን የጣልያን ወታደሮች ግንባር ግንባራቸውን እያሉ ያሰተኗቸው ጀመር። እንዲህ ከየት አቅጣጫ እንኳን እንደሚተኮስባቸው ያላወቁት ጣልያኖች መላ ቅጡ በጠፋ ሁኔታ ሲርመሰመሱ አልመው ተኳሾቹ የአቢቹ ተዋጊዎች አንድ በአንድ ለቀሟቸው።

አደጋ የደረሰበት ይኼ ሁለት ሻለቃ ጦር ስለሁኔታው በራዲዮ ለአለቆቹ ቢያሳውቅም፣ የጣልያኖቹ አጋዥ ጦር ከስፍራው ከመድረሱ በፊት እነ አቢቹ ከዚያ ሁለት ሻለቃ ጦር ለወሬ ነጋሪ ሳያስቀሩ ሊነጋጋ ሲል የቻሉትን ያህል ንብረት ዘርፈው፣ የተረፈውን ለሽፍቶች ትተው እንደ አመጣጣቸው ማንም ሳያያቸው ተሰወሩ።

ይኼ ማርሻል ባዶለዮን ያስለቀሰ፤ ለሰሚው ማመን የሚያስቸግር ጀብዱ የአቢቹ ጦር እንደሠራው ጥርጥር የለውም። ለዚህም ጠዋት ከድንኳኔ ስወጣ ከደጃፍ ያገኘኋቸው በርካታ የሲጋራ ፓኮዎችና ሁለት ሳጥን ሙሉ የጣልያን ቪኖ ምስክሮች ናቸው። ሁሌም እነ አቢቹ በለስ ሲቀናቸው የሚዘርፉትን የጠላት ንብረት፣ ጦርና የምግብ ቁሳቁስ ሁሉ ሌሊት አምጥተው ለዋናው ጦራቸው ያከፋፍሉ ነበር።

ታዲያ እነ አቢቹ በዚህ መልኩ ትግላቸውን አፋፍመው ሳለ አንድ ሌሊት ከትግራይ ሽፍቶች ጋር ችግር ገጠማቸው። የአቢቹ ጦር እንደ ወትሮው ሌሊት ቢያንስ ሁለቴና ሦስቴ ሰፈሩን እየቀያየረ ሲንቀሳቀስ፣ የትግራይ ሽፍቶች አንድ አሰቸጋሪ መንገድ ላይ አግኝተውት አናሳልፍም በማለት በከፈቱበት ተኩስ ሽፍቶቹ የአቢቹን ሁለት ተዋጊዎች ይገድላሉ።

አቢቹ መጀመሪያ ልክ ችግሩ እንደተፈጠረ ከሽፍቶቹ ጋር ተደራድሮ ለማለፍ ቢሞክርም ሽፍቶቹ አንዲት መንደር ውስጥ መሽገው አናሳልፍም ብለው በከፈቱት ተኩስ ሁለት ተዋጊዎቹን ሲገድሉበት፣ አቢቹ ትዕግሥቱ አልቆ መጀመሪያ ሽማግሌዎች፣ ሴቶችና ሕፃናት መንደሯን ለቀው እንዲወጡ ለሽፍቶች ያቀረበው ጥያቄ አዎንታዊ መልስ አግኝቶ አዛውንቶች፣ ሴችና ሕፃናት መንደሯን ልክ ለቀው እንደወጡ ያቺን የሣር ጎጆ የሞላባትን መንደር በእሳት አጋያት። ከዚያ ከየመሸገበት እየወጣ ሽሽት የጀመረውን ሽፍታ እያሳደደ ቀጠቀጠው።

ምንም እንኳን እነዚህ መንደራቸውን ለቀው እንዲወጡና ነፍሳቸውን እንዲያድኑ የተፈቀደላቸው አዛውንቶች፣ ሴቶችና ልጆች ንጋት ላይ ጦር ሰፈራችን ደርሰው ስለሁኔታው ለሹሞች አስረድተው ደጃዝማች አበራ በፊታውራሪ ሙሉ የሚመራ ጦር ወደ መንደሯ ቢልክም፣ የፊታውራሪ ሙሉ ጦር በቦተው ያገኘው ነገር ቢኖር የመንደሯን አመድና እዚህም እዚያም የወደቁ የሽፍቶችን ሬሰ ብቻ ነበር።

ከዚህች ቀን ጀምሮ እስካሁን በታላቅ ኩራት ሽንጣቸውን ገትረው ከራስ ካሣ ጋር ይከራከሩለት የነበሩትን ራስ ሥዩም መንገሻን አጣ። መንደር ማቃጠል ከጀመሩ ከጣልያኖችና ከሽፍቶች በምኑ ይሻላሉ? እያሉ ክፉኛ አማረሩ።

በኛም መንደር ስለ አቢቹ ሁላችንም የተለያየ አስተሳሰብ መያዝ ጀመርን። ከአንደኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ የጦር ሜዳዎች የዋለው ኮሎኔል ኮኖቫሎቭ መቶ በመቶ የአቢቹ ደጋፊ ሲሆን፤ ደጃዝማች አበራም ውስጥ ውስጡን በሆዱ አቢቹን ቢደግፍም እንደ ጦር አዛዥነቱ አቢቹን በአደባባይ ሳይደግፍም ሌላም አስተያየቶች ሳይሰጥ ዝም አለ። እኔም የራስ ካሣ የጦር አማካሪ እንደመሆኔ መጠን፣ ምንም እንኳን የአቢቹ ጀግንነት ፍጹም ቢያኮራኝም፣ መንደር ማቃጠል ብቻ ሳይሆን እንዲህ በታላቅ ወኔና ድፍረት የጣልያኖቹን የጦር ሠፈር ሰብሮ እየገባ የሚጥለው ትልቅ አደጋ ጣልያኖችን እጅግ በጣም አስቆጥቶ፣ ሌሊት በተደፈሩ ቁጥር ቀን በነዚያ የሰማይ ላይ አሞራዎች የሚያዘንቡት የሞት እሳት በየቀኑ ፍጹም አረመኔያዊነት የተሞላበት እየሆነ እንዲመጣ ትልቁ መንሥኤ አቢቹ እንደሆነ ስረዳ መላው ጠፍቶኝ እኔም ዝም ማለትን መረጥኩ።

ኮሎኔል ኮኖቫሎቭ አቢቹ በፈለገው የጦር ሜዳ፣ በመረጠው ሰዓትና ቦታ የጠላትን ጦር መጨፍጨፍ የተቀደሰ፣ በእግዚአብሔር የተሰጠው ቅዱስ መብቱ ነው ብሎ ያምናል።

-----------------/////------------------

## አብቹ

### ክፍል ሁለት

አዎ ነገሩ የሆነው ያኔ ልጅ ተድላ በተስቦ በሽታ በድንገት የሞተ ሰሞን ነው። በዚያን ሰሞን ከሁለቱ ራሶች ዘንድ በተደጋጋሚ እኔ፣ ኮሎኔል ኮኖቫሎቭና ደጃዝማች አበራ ተጠርተን በተደጋጋሚ ልጁን እንድናቆመው ትእዛዝ ተሰጠን። ግን አቢቹን ማቆምና ወደ ጦሩ እንዲመለስ ማድረግ ማናችንም አልተቻለንም ነበር። ታዲያ አንድ ቀን ቀኛዝማች ሼክ ሁሴን አባወርቂ በጣም ተቆጥተው ወደኔ መጡና የሆነ ምሥጢር ነገሩኝ። እኔም እሳቸውን ይዤ ኮሎኔልን አስጠራሁና ከደጃዝማች አበራ ዋሻ ተሰብስበን መምከር ያዝን። ቀኛዝማች ሼክ ሁሴን አባውርቂ የሰሙትን መሥጢር ለደጃዝማች አበራ ሲነግሩት ያለወትሮው በጣም ተበሳጭቶ በከፍተኛ ድምጽ "ሊሆን አይችልም!" እያለ ጮኸ።

ነገሩ እንዲህ ነበረ። ልጁ ዝናው እየሰፋ፣ ቀን በቀን የጦሩ ቁጥር እየጨመረ ሄዶ፣ እንዲየውም በመጨረሻ ሰዓት ላይ አንድ ሀብቶም በሚባል የሀማሴን ልጅ የሚመራ ወደ

300 የሚሆኑ የኤርትራ ተወላጅ ወታደሮቹን ይዞ ከልጁ ጦር ጋር ተቀላቀለ በተባለበት ሰሞን የትግራይ መንደሮች ከመቼውም ጊዜ በላይ መጨስ ጀመሩ። እናም ይኼ ወሬ ከሁለቱ ራሶች አልፎ ከአፄው ጆሮ ይደርስና አፄ ኃይለሥላሴ በራዲዮ ለሁለቱ ራሶች ቀጭን ትእዛዝ ይሰጣሉ፤ ያም "ልጁን አቁሙት" የሚል።

አዎ አፄው፣ ንጉሠ ነገሥቱ፣ አሁንም ጦርነቱን በሰላም እፈታለሁ ብለው ተስፋ ያደርጉ ስለነበር፣ እንዲህ እንደ አቢቹ ዓይነት አርበኞች የጠላትን ጦር ድንገት እየደረሱና አደጋ እየጣሉ፣ የገደሉትን ገድለው፣ የዘረፉትን ዘርፈው እንዳመጣጣቸው ድንገት ውልቅ የሚሉት ነገር፣ አፄው አሁንም ተስፋ በሚያደርጉት ሰላም እንቅፋት እንዳይሆንባቸው በመስጋት በቀጭኑ ትእዛዛቸው "ልጁን አቁሙት" ብለው ሁለቱን ራሶች አዘዟቸው።

በአርበኛው የልጁ ጦር ላይ የሁለቱ ራሶች ጦር ሊዘምትበት እንደተዘጋጀ ነበር ቀኛዝማች የሰሙት ምሥጢር የሚያስረዳው። እና ከብዙ ውይይት በኋላ አቢቹን በዘዴ ወደ ደጃዝማች አበራ የጦር ሠፈር አምጥተን አስረንም ቢሆን ልናሰቀረው አሰብንና ምክንያት ተፈጥሮ መልእከተኛ ልንልክበት፣ መልእከተኛውም አቢቹ የሚያምነው ሰው የቅርብ ጓደኛው አንበሳ እንዲሆን ተወሰነ።

መጀመሪያ አንበሳ ዋሽቶ አቢቹን በማስያዙ ለመተባበር ፈቃደኛ አልነበረም። በኋላ ላይ ደጃዝማች አበራ ለብቻ ወስዶ "አንበሳዬ እይማ! እኔ ጤነኛ አደለሁ? አሁን አቢቹ ጠላቱ ስለበዛ ከበው ሳይገድሉት በፊት ሄደህ፣ አበራ በሞት አፋፍ ላይ ነውና ቶሎ ድረስ ብትለው በኔ አይጨክንምና ቶሎ ይመጣል። ከዚያ መክሬም ለምኜም ቢሆን እዚሁ አስቀረዋለሁ" ብሎ ደጃዝማች አንበሳን ካሳመነው በኋላ ወደ አቢቹ፣ ወደማይታወቀው "የልጁ የጦር ሠፈር" ላክነው።

አዎ አንበሳ ለአቢቹ መልእክቱን በትክክል እንደሚያደርስና አቢቹም የጦር አለቃው በሞት አፋፍ ላይ ሆኖ ሲጠራው ሳይውል ሳያድር እንደሚመጣ እርግጠኛ ሆነ። አቢቹ ጨለማን ተገን አድርጎ ማታ ሲመጣ እያንዳንዳችን ምን ምን ማድረግ እንዳለብን ስንወያይ በጠራራው ፀሐይ አቢቹ ድንገት ከች አለ። ሽብጥ ጫማ የተጫማ፣ አጭር ቁምጣ ታጥቆ በጣም ሰፋ ያለ እጅጌ ጉርድ ኮቱን በወታደር ቀበቶ ጥፍር አድርጎ ያሠረ ጨበሬያም ልጅ ድንገት ከዋሻው ዘው ብሎ ገብቶ ከአንዱ ጥግ ሲቆም፣ በዚያች ዋሻ ውስጥ ያለን ሰዎች ሁሉ አፋችንን ከፍተን ቀረን። አቢቹ ነበር።

መሣሪያ አልታጠቀም፣ ግን በዚያ ሰፋ ባለና በወታደር ቀበቶ ጥበቅ አድርጎ ባሠረውና ቡፍ ባለው ኮቱ ውስጥ ሽጉጡን እንደወሸቀ ጥርጥር የለውም። እንዲህ ሁላችንም ተደናግጠን ዝም እንዳልን ደጃዝማች አበራ አሽከሩን በዓይኑ ጠቀስ ሲያደርገው አሽከርዬው ሹልክ ብሎ ወጣ። የአሽከርዬው አወጣጥ ከዋሻው ደጃፍ ላይ ዘብ የቆሙትን ወታደሮች ለመጥራት እንደሆነ ሁላችንም ገብቶናል። እርግጠኛ ነኝ ከአሳሳቁ አቢቹም በደንብ ገብቶታል። ብዙም ሳይቆይ አሽከርዬው እጆቹን ወደላይ አንሥቶ ከጀርበው መሣሪያ ተደግኖበት ወደ ዋሻው ተመለሰ። አሁን አቢቹ ከዋሻዋ ውጪ ኃይል እንዳለውና በደንብ አስቦበት እንደመጣ ሁላችንም በዚያች ዋሻ ውስጥ ያለን ሰዎች ገባን።

“ምርኮኛ መሆናችን ነው እንዴ አቢቹ? “ ሲል ኮሎኔል ኮኖቫሎቭ እንደተቀመጠ አረቄውን በትንፋሽ ጨልጦ ጠየቀው። “በፍጹም! ኮሎኔል በፍጹም! ማን የማን ምርኮኛ ይሆናል ጌታው?” ሲል መለሰና ወዲያው ቀጥሎ “ለምን ግን ደጃዝማች? ለምን?” ሲል ደጃዝማችን ጠየቀ። አሁን ደጃዝማች ትንሽ አሰብ አድርጎ፣ ሁለቱ ራሶች ያሰቡለትን ድግስ ፍርጥርጥ አድርጎ አስረዳው።እንዲህ ደጃዝማች አቢቹን ሲያስረዳው አቢቹ በዝምታ ያዳምጥና “ግን ለምን? ግን ለምን?” እያለ በተደጋጋሚ ይጠይቃል።

የአዜውን ፍላጎት ኮሎኔልም፣ እኔም በወግ በወጉ ልናስረዳው ሞከርን። ይሁን እንጂ የአቢቹን “ግን ለምን?” ጥያቄ መመለስ የቻለ ሰው አልነበረም። አቢቹ ተሰናብቶን ከመሄዱ በፊት ግን አንድ እስከ ሕይወቴ መጨረሻ ድረስ የማልረሳው አጭር ንግግር አድርጎ ነበር።

> ደጃዝማች፣ ገና ከሰላሌ ስንነሳ ታማኝነቴን በምኒልክ ስም ቃል የገባሁት ላንተ እንጂ ለሽማግሌዎች ወይም ለንጉሡ አደለም። እኔ ንጉሥ አደለሁም፣ ተራ ወታደር እንጂ። እና እኔ ሁለት ሦስት ወር ደሴ ተጎልቼ ጣልያኖች እጄን አስኪይዙኝ አልጠብቅም። ላንተ ግን አሁንም በምኒልክ ስም፣ በምኒልክ አምላክ በድጋሚ ቃሌን እሰጣለሁ። ለአንተ እሞታለሁ። ተመለስ ላልከው ግን፣ የት ነው የምመለሰው? ምንስ መመለሻ ቤት አለኝና? እዚህም እዚያም እሳት እየነደደ እንዴት ቁጭ ልበል? ሽማግሌዎቹ ጦር ሊሰዱብኝ አስበው ከሆነ ደግ፣ ምንም ችግር የለም። ግን እኔ ከነሱ ጠብ እንደሌለኝና የሀገሬ ታማኝ ወታደር እንደሆንኩ አስረዳልኝ። ደጃዝማች፣ ሰማኝማ! ምናልባት ካልተገናኘን እማማን ደስተኛ እንደነበርኩ ንገራት በእሳተጎሞራ መኻል ማለፍ ቢኖርብኝም ወደ ሰላሌ እመለሳለሁ” ነበር ያለው።

አዎ፤ በምኒልክ ስም ቃል የገባ ኢትዮጵያዊ ቃሉን እንደቅዱስ ቃል ስለሚቆጥረው ፈጽሞ አይሽረውም።

ምንም እንኳን ጣልያኖች ዘመኑ ያፈራውን ምርጥ መሣሪያ የታጠቁ፣ በቁጥሩ እጥፍ የሚሆን ጦርና በብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች፣ በታንኮች፣ በመድፎችና በአውሮፕላኖች የሚታገዙ ቢሆንም እንዳሰቡት የራስ ካሣን ጦር በተንቤን በብረት አጥር አሥሮ ብትንንኑን ለማውጣት ሳይቻላቸው ቀርቷል።

የኢትዮጵያ ጦር በትንንሽ ቡድኖች ተከፋፍሎና ተበታትኖ የየራሱን ቀኛዝማች፣ ግራዝማች፣ ባላምበራስና ሹም ተከትሎ ወደ ዋናው ዓላማው ወደ አሸንጌ ሐይቅ እየገሰገሰ ነው። የልጁም ጦር አሁን ከምን ጊዜውም በላይ ተጠናክሯል። በርከት ያሉ ሹሞቻቸው በየጦር ሜዳው የወደቁባቸው ወጣት ወታደሮች ከጅግነውና ከጀብደኛው የአቢቹ ጦር ጋር ከመቀላቀላቸውም በላይ በርካታ ምርጥ የትግራይ ልጆችን ያቀፈ ጦር ስለነበረ ያለምንም ካርታ በቀላሉ የሚንቀሳቀስና ሴቶች፣ ልጆችና አዛውንቶች የሌሉበት፣ ከግማሽ በላይ የሚሆነው ጦሩ በራሱ ፈረስ የሚንቀሳቀስና፣ በጣሊያኑ ጦር ላይ ድንገት ባልታሰበ ሰዓትና ቦታ ደርሶ አደጋ የሚጥልና እንደአመጣጡ የሚሰውር ጦር በመሆኑ ጣልያኖች ክፉ ቂም ከያዙበት የኢትዮጵያ ጦር አንዱ ነበር።

የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ሰዎችማ ይኼን አንበሳ ጦር እንዴት እንደሚንቀጠቀጡለት እግዜር ብቻ ነው የሚያውቀው። ምንም እንኳን ይኼ የከፋው ጦር ማለትም ዋናው የልጁ አቢቹ ጦር ታማኝነቱ ለሰላሌው ለደጃዝማች አበራ ጦር ቢሆንም፣ ይኼ ጦር፣ ጦር ከሆነበት ቀን ጀምሮ እስካሁን ከማንኛውም ደጃዝማችም ሆነ ከሁለቱ ራሶች ምንም ዓይነት ትእዛዝም ሆነ መመሪያ ተቀብሎ የማያውቅ፣ ከጣልያኖችና ከደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ሠራዊት በሚዘርፈው ንብረት ሠራዊቱን የሚያስተዳድር ጦር ነው።

ይኼ የአቢቹ ጦር ለሁለቱ ራሶች "ተራ የጥጋበኛ ሽፍቶች ክምችት" ነው። ጃንሆይም ቢሆኑ "ይኼ በአንድ ባለጌ ወጣት የሚመራ ጦር" ለሁለቱ ራሶች በተለይም ለራስ ካሣ በተደጋጋሚ ባስተላለፉት ትእዛዝ አሻፈረኝ በማለቱና ሁለቱ ራሶች ልጁን ወደ እናት ጦሩ ለመመለስ ያደረጉት ያላሰለሰ ጥረት ውጤት አልባ በመሆኑ፣ ጃንሆይ በአቢቹና በጦሯ ላይ ሳይቆጡ አልቀሩም።

በኋላ ላይ እንደሰማሁት ይኼ ጀግናውና ጀብደኛው የአቢቹ ጦር አወቃቀር ይፋ ባይሆንም በአራት ጄኔራሎች የሚመራ ነበር።

1ኛ በጄኔራል ሀብቶም የምመራ የሀማሴን ልጆች ጦር፣

2ኛ በጄኔራል ተስፋጽዮን የሚመራው የትግራይ ልጆች ጦር፣

3ኛ በጄኔራል ጋሹ የሚመራው የጎጃም (ዳሞት) ልጆች ጦር፣

4ኛ በጄኔራል ወርቁ የሚመራው ዋናው የሰላሌ ልጆች ጦር ሲሆን እነዚህ አራት ጄኔራሎች ከነጦራቸው ታማኝነታቸው ለልጁ ለአቢቹ ነበር።

እናም እነሆ ለመጀመሪያ ጊዜ ይኼ ጦር ወደ አሸንጌ ጦር ወደ አሸንጌ ሐይቅ እንዲውርድ ከደጃዝማች አበራ ቀጭን ትእዛዝ ሲደርሰው ትልቅ ፈተና ላይ ወደቀ። እነዚህ አራት ጄኔራሎችና መሪያቸው አቢቹ አንድ ሌሊት ሙሉ ሲመክሩ አድረው በመጨረሻ ባላራት ነጥብ ውሳኔ ላይ ደረሱ።

1ኛ የትግራይ ልጆች ጦሩን እያገዙና መንገድ እየመሩ ወደ አሸንጌ ሐይቅ ወርደው ከዚያ ወደየቀበሌያቸው እንዲመለሱ፣ 2ኛ የጎጃም (ዳሞት) ልጆች ከአሸንግጌ ሐይቅ በኋላ ወደዳሞት የሚመለሱበትን ሁኔታ አሸንጌ ሐይቅ ላይ እንዲመከርበት፣ 3ኛ የሰላሌ ልጆች ጦር የደጃዝማች አበራን ጦር ተከትሎ ወደ ሰላሌ እንዲመለስ

4ኛ መመለሻ የሌለው የሀማሴኑ ጦር ከሰላሌው ጦር ጋር ተቀላቅሎ የዚህ ጦር እጣ ፋንታ ተካፋይ እንዲሆን ተስማምተው፣ የደጃዝማች አበራን ትእዛዝ ተቀብለው ከደጃዝማች መሸሻ የከንባታው ጦር መሪ ጋር ጎን ለጎን የጠላትን ጦር እያርበደበዱ ወደ አሸንጌ ሐይቅ ወረዱ።

ከቀትር በኋላ ነው፣ ፀሐይዋ ግን አሁንም እንደ እሳት ትፋጀለች። አንድዳ አንድዳ ነፍሳችንን ልታወጣው ነው። ይኸው 10 ሰዓት ሙሉ ያለ ውሀ በመንገድ ላይ ነን። አሥር

ሰዓት ሙሉ በዚህች በረሃማ ቀበሌ ለእፎይታ ያህል እንኳን ወገባችንን ሳናሳርፈው የደከሙ እግሮቻችንን እየጎተትን በጉዞ ላይ ነን። ብቸኞች፣ ሁለትም ሦስትም ሆነው በጓድ ያሉ፣ በቡድን በቡድን ሰብሰብ ያሉ መንገዱና ጉዞው ካቅማቸው በላይ ሆኖባቸው አንዲት እርምጃ ወደፊት ማለት ያልሆነላቸው ወታደሮች፣ በዚያች በራሃማ ቀበሌ ተበትነው በበቀሉ የግራር ዛፎች ጥላ ሥር ጋደም ብለዋል።

እነዚህ ምስኪን ወታደሮች እንዲህ በየግራሩ ጥላ ሥር ጋደም ሲሉ እንቅልፍ ይዟቸው ጭልጥ ይልና ራሳቸውን አደጋ ላይ ይጥሉታል። ብዙ ጊዜ እንዲህ እንደማሽላ ቆሎ ተበትነው በየግራሩ ሥር ባረፉበት የጨካኞቹ ሽፍቶች ካራ ለዘላለም አስተኝቷቸዋል። ይኼ አረመኔያዊ የሽፍቶች ጭካኔ ሊደርስበት እንደሚችል ቢገምትም እድሉን በፈጣሪ ላይ ጥሎ ገደም ይላል። በዚህ መልኩ ስንኳትን ውለን በአንድ ወጣት ፊታውራሪ ከሚመራ ጦር ጋር ተቀላቀልን።

ከዚሁ ወጣት ፊታውራሪ ጦር ጋር ስንጓዝ ውለን ማምሻው ላይ ከአንድ ከደረቀች ወንዝ ዳርቻ ደረስን። ወታደሮቻችን እዚያች የደረቀች ወንዝ መኻል ገብተው በእጃቸው ትልቅ ጉድጓድ ቆፈሩ። በዚህች ጉድጓድ ውስጥ ትንሽ ውሀ አስኪጠራቀም ድረስ እንደ እድሜ ልክ የፈጀ ጊዜ ፈጀ። እኛ ቁጥራችን ብዙ ነውና ከዚያች በመከራ የተራቀመች የደፈረሰች ውሀ ለመጨረሻው ወታደር የደረሰው ነገር ቢኖር ውሀ ሳይሆን ጭቃ ብቻ ነበር። ጀንበር ጠልቃ ብዙም ሳይቆይ የተንቤን መጨረሻና የአበርጋሌ አዋሳኝ ከሆነቸው የአረንቋ ወንዝ ዳርቻ ደረስን። እፍኝ የሽንብራ ቆሎዬውን በልቼ ውሀ ሳልጨርስ፣ ጉንጭ ውሀዬን አጣጥሜ ሳልጨልጥ ነጋሪቶች መጎሰምና ጡሩምባዎች መነፋት ጀመሩ። የኼ ደግሞ ወደፊት በል ማለት ነውና እኛም ከጦሩ ጋር ተቀላቅለን የደከሙ እግሮቻችንን ወደፊት አልናቸው። ኮረም ደረስን።

በኮረም የጦር ሠፈር መሽተሸት ሲል የገበሬው ወታደር ማለትም አባቱን፣ ወንድሙን፣ ጓደኛውን፣ በተንቤኑ የጦር ግንባር የመቅበር ዕድል እንኳን ያልገጠመው የከፋው፣ ሆድ የባሰው ወታደር፣ እሳት አንድዶ እየሞቀና የቆላትን ሽንበራውን እየቆረጠመ፣ በማሲንቆ እየተደገፈች የምትንጎራጎረውን የአንድ የሰላሌ ልጅ ሙዚቃ ማዳመጡን ተያይዞታል። አንጀት የምተበላዋ የማሲንቆ እንጉርጉሮ ስለ ልጁ ስለ አቢቹ ነበረች።

አቢቹ ደራ ደራ ………………………… ……………………………..

አቢቹ ደራ ደራ ………………………… ………………………………

ዛሬ አዝማሪው ሳይቀር ስለራሶቹ ጀግንነት፣ ስለ ንጉሠ ነገሥቱ ታላቅነት ማንጎራጎሩን እርግፍ አድርጎ ትቶታል። የአቢቹ ዝና ታዲያ ጃንሆይ ዘንድ ደርሶና እርሳቸውም ተቸግርውበት ኖሮ ጃንሆይ ለመጨረሻው ወሳኝ ውጊያ ወደ ኮረም መጥተው በተፈጥሮ ምሽግ ውስጥ አርፈው ከጦር መሪዎቻቸው ጋር ሲመክሩ በነበረበት ወቅት ስለአቢቹ "ይቺ አንድ ፍሬ ደጃዝማች፣ ከኛ በላይ ጀብዱ አየሠራች መሆኑን እንሰማለን!" ብለው ነበር።

"አንድ ፍሬ ደጃዝማች!" ሲሉ ጃንሆይ ለአቢቹ ማዕረግ መስጠታቸው ይሆን? አቢቹ በጃንሆይ ልብ ውስጥ በእንዲህ ዓይነት የገባችው ለምን ይሆን?

አቢቹ ምንም እንኳን በዚህ ጦርነት በጦር ሜዳ የወደቁት ሁለት ወንድሞቹ ብቸኛ ወራሽና በማዕረግም ፊታውራሪ ቢሆንም፣ ምንጊዜም ሕጋዊውን የማዕረግ ስሙን ተጠቅሞ አያውቅም። አቢቹ በደጃዝማች አበራ የሚመራው የሰላሌው ጦር አባልና ለመሪው ለደጃዝማች አበራ ታማኝ ቢሆንም፣ የራሱን ጦር እየመራ ከሰላሌው ደጃዝማች አበራ የጦር ሠፈር ርቆ ከጠላት ጦር በሚዘርፈው ንብረት ጦሩን የሚያስተዳድር፣ በብዙዎቹ ዘንድ በሁለቱ ራሶች ሳይቀር እንደ ተራ ሽፍታ የሚቆጠር ለከዳተኛውና ለባንዳው ለደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ጦር የእግር እሳት የሆነ፣ ምንም እንኳን በርከት ያሉ በሀብቶም የሚመሩ የኤርትራ ልጆች የተቀላቀሉበትና የትግራይና የዳሞት ልጆችንም ያቀፈ ጦር ቢሆንም፣ አብዛኛው ጦሩ የሰላሌ ልጆች የሞሉበት ሲሆን፣ ጦሩ ምንም ዓይነት የማዕረግ ስም አይጠቀምም ነበር።

ከከንባታው መሪ ከደጃዝማች መሸሻ ቀብር በኋላ አንድ የከንባታ ልጅ ስለ አቢቹ ያጫወተኝ ባጭሩ የሚከተለውን ይመስላል። "የከንባታው ጦር በጣልያን ሠራዊት ተከቦ፣ መውጫው ጠፍቶት፣ አጥፍተህ ጥፋ ዓይነት ውጊያ ላይ እያለ ከየት መጡ ሳይባል እነዚያ የአቢቹ ፈጥኖ ደራሽ ደቦል አንበሶች ከጣልያኑ ጦር ብብት ውስጥ ገብተው ሲኮረኩሩት፣ ደመሰስኩ ብሎ የሚኩራራው የጣልያኑ ጦር ሳያስብ አደጋ ደርሶበትና በተራው ሲያፈገፍግ የከንባታውን ጦር ከዚያ ካለቀለት ውጊያ ውስጥ እነቢቹ መንጥቀው አወጡት።"

4ኛው ረድፈኛ/ 4ኛው ክፍለ ጦር ከንባታዎችን ጨምሮ የበርካታ የሸዋ ደጃዝማቾች ጦር ሕብረት ነበር። ከመሪዎቹ አንጋፋዎቹ ሽማግሌው ደጃዝማች ወንድይራድ፣ ወጣቱ ደጃዝማች አበራ የሰላሌው፣ ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ፣ የዋጎች ወራሽ ሲገኙበት፣ መሪያቸውን ያጡት የከንባታ ልጆች ከጀግናው የአቢቹ ጦር ጋርና የሌሎችም ደጃዝማቾችን ጦር ያካተተው ጠንካራ ጦር፣ በዚህ ጦርነት ኢትየጵያ በጦር ግንባር ካሳለፈቻቸውና በጦርነት አውድማ ካዋለቻቸው፣ በጦርነት እሳት ከማገደቻቸው ምርጥ ልጆቿ፣ የደጃዝማች አበራ፣ የደጃዝማች ወንድይራድ፣ የደጃዝማች ኃይሉ ከበደ፣ የልጁና የከንባታ ልጆች በታላቅ ወኔና ቆራጥነት ታላቅ ጀብዱ ሲሠሩ ታይተዋል። በዚች የጨረሻዋ ቀን ወሳኝ ጦርነት የአቢቹ ጦር ጄኔራል ወርቁ አባቱን አጥቷል። ቀኛዝማች ሼክ ሁሴን አባወርቁ ከልጃቸው ጋር ጎን ለጎን ከጠላት ጋር ሲዋጉ ከጀርባቸው የተተኮሰችን ጥይት በደረታቸው ተቀብለው ልጃቸውን በማዳን የጀግና ሞት ሞተዋል። አባቱን ያጣው ወርቁ የቆሰሉ የትግል ጓዶቹን ሲደግፍ፣ ሲራዳና ሲያስተባብር ማየት እጅጉን በጣም ያኮራል። አምስቱ ጀኔራሎች ሀብቶም፣ ተስፉ ጽዮን፣ ጋሹ፣ ወርቁ እና አቢቹ በህብረት ጠላትን ሲያከታልቡት ማየት እንደሁም እንዲያ ምድር ቀውጢ ሆና አሸናፊውና ተሸናፊው ባልታወቀበት ሰዓት፣ ፈረሴ አንገቱን በጥይት ተመቶ ሲወድቅ እኔን ከኮረቻው ላይ አስፈንጥሮ ጥሎኝ ራሴን ስቼ በወደቅኩበት መነሣት አቅቶኝ ስጣጣር ሁለት የአቢቹ ፈረሰኛ ጦረኞች ጎን ለጎን ሽምጥ ጋልበው መጥተው ማጅራቱን ጨምድደው እየጎተቱ ወስደው ካስተማማኝ ቦታ እንደጣሉኝ ሳውቅ ኢትየጵያውያን ጀግኖች ብቻ ሳይሆን በፍቅር የተሞሉ መሆኑን አረጋገጥኩ።

ወርቁ በዛሬው ጦርነት በጣም የሚወዳቸውን አባቱን ቢያጣም የቆሰሉና የደከሙ የጦር ሜዳ ወንድሞቹን በመርዳቱ አልቦዘነም። ሀብቶም ግራ እግሩን ቢመታም በጠፍር ግጥም አድርጎ አሥሮ የተረፉ ወታደሮቹን ያሰባስባል። አቢቹ በሁለት ጥይት ትከሳውን ቢመታም ቁስሉን እንኳ ለማሠር ሳይሞክር ጥላሸት በሚመስለው ጥቁር ፈረሱ ላይ ሆኖ ወዲህ ወዲያ እየተዘዋወረ ጦሩን ያሰባስባል። ተስፋ ጽዮንና ጋሹ በማይጨው የዛሬው ጦርነት ታሪክ ሊጽፈው የሚገባ ጀብዱ ሲሠሩ ውለው በአምባ ሆራ የጦርነት አውድማ ወድቀዋል።

በጨበጣ ውጊያ ከኢትዮጵያ ጀግኖች ፊት ጠላት መቆም አልቻለም። በየጭፍራው የተሠማራው ጦር ጠላትን ሲያይ እያጓራና እየፎከረ የጠላትን እሬሳውን ካልሆነ ሜዳ ላይ አያስቀረውም፤ ከወገን ሠራዊት ጠላትን አይቶ ወደኋላ የሚመለስ የለም። በኮረም፣ አምባላጌ፣ መቀሌ፣ ማይጨውና ሌሎች አውደ ውጊያዎች እንደንብ የበዛው ዘማች እንደ አንድ ዘንዶ ተምዘግዝጎ ጠላትን ሲቆላው ጠላት አለቀለት ሲባል፣ ታዲያ ምን ያደርጋል እነዚያ የተረገሙ የሰማይ አሞሮች ከአየር መርዝና የቦምብ ናዳ ያወርዱበታል። የወገን ጦር መስዋዕትነቱን ከፍሎ የተረፈው ጠላትን ቀንና ሌሊት ሲያሳድድ  በፈንጂ በታጠረ ምሽግ ውስጥ ያለው ጠላት ብቻ ነፍሱ ይተርፋል።

በዛሬው ጦርነት ብዙ ቂም የተያዘበት የአቢቹ ጦር እጅጉን ተጎድቷል። ሁለት ምርጥ አዋጊና ተዋጊ ጄኔራሎቹን ከማጣቱም በላይ ሁለት ሦስተኛው የሠራዊቱ አባል በማይጨው የጦርነት አውድማ ለእናት ሀገሩ አጥንቱን ከስክሶ፣ ደሙን አፍስሶ፣ በጠላት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል።

ማምሻው ላይ የሁለቱን ደቦል አንበሶች ሬሳ ጀግኖቹ ከጦር ሜዳ አምጥተው አንድ ሰዓት ባልሞላች ዋይታና ለቅሶ በሌላት የቀብር ሥነሥርዓት ከአንዲት በጣልያኖች ቦምብ ግማሽ አካሏ ካረረች ዋርካ ሥር በታላቅ ክብር ቀበሯቸው። ጎን ለጎን ከጠላት ጋር እንደተዋጉ ሁሉ ጎን ለጎን እከመጨረሳው ተቀበሩ።

የደጃዝማች አበራ የሰለሌው ጦር በዛሬው ጦርነት ሦስት ጊዜ የጣልያኖቹን ምሽግ ሰብሮ ገብቶ እጁ እያስገባ፣ እንደገና ሦስት ጊዜ እንደዚያ ያንን ከባድ መስዋዕትነት የከፈለበበትን ለቅቆ መውጣት ተገዷል። በዚህ ጦርነት ሦስት አራተኛው የሰላሌዎቹ አሉ የሚባሉት ቆራጦቹ፣ ጀግኖቹና ደፋሮቹ ልጆች ከማይጨው የጦር ሜዳ ከአምባ በሆራ አልተመለሱም። እሰከመጨረሳው ድረስ ከጠላት ጋር ጉሮሮ ለጉሮሮ ተናንቀው በየምሽጉ ጠላትን እየገደሉ ወድቀዋል።

ጃንሆይ ከማይጨው ጦር ሜዳ ተመልሰው አዲስ አበባ ከመግባታቸው በፊት ከመኳንንቶቻቸው ጋር የመጨረሻውን የጦር ምክክር ሸንጎ ያካሄዱትና የመከሩት ፍቼ፣ ሰላሌ ውስጥ ነበር። ኮሎኔል ቀኑን ሙሉ ከአንዲት ጉብታ ላይ ተቀምጦ ዙሪያ ገባውን ጦር በአይኑ እየፈለገ እንደሆነ ገብቶኝ ወደተቀመጠባት ጉብታ ሂጄ፣ “ታዲያስ ኮሎኔል፣ አቢ የምትመጣ ይመስልሃል?” ብዬ ላቀረብኩለት ጥያቄ፣ ከተቀመጠባት ጉብታ ላይ እየተንፏቀቀ ወርዶ ቆመና አሁንም እየዞረ ዙሪያ ገባውን መጨረሻ የሌለው የሚመስለውን የሰላሌን ሜዳ አየት አድርጎ፣ “ይመስለኛል፣ መምጣትም አለበት፤ የሱ እገኛ ወታደሮች

እኩለ ቀን ላይ በትንሽ በትንሹ ቡድን እየሆኑ ወደ ጃርሶ መስመር ሲውርዱ አይቻለሁ። ምናልበትም እስኪመሽለት እየጠበቀ ሊሆን ይችላል እንጂ ይመጣል። እንዲህማ ከዚህ ሁሉ መከራ በኋላ በትውልድ ሀገሩማ ሳይሰናበተን" ብሎ ኮሎኔል ሊናገር የፈለገውን ሳይጨርሰው የጃንሆይ መልእክተኛ መጥቶ ጃንሆይ እንደጠሩን ስለነገረን ጊዜ ሳናጠፋ ወደ ጃንሆይ ሄድን። ጃንሆይ ጋር ባሳለፍናት ጥቂት ቆይታ ጃንሆይ እኛ ለእሳቸውና ለምስኪኗ ኢትዮጵያ የዋልነውን ውለታ ምንጊዜም የማይረሱትና ከፍለው የማይዘልቁት ባለውለታቸው እንደሆንን አመስጋግነው ተሰናበቱን።

የአቢቹ ጦር በቆርበቶው ጦርነት ከፍተኛ ጉዳት እንደደረሰበት ሁላችንም ሰምተናል። ጃንሆይ ሳይቀሩ አሻፈረኝ ልጄን ብቻውን ጥለን አንሄድም እስከማለት ደርሰው ነበር። እንደዚያም ሆኖ ጦሩ ከፍተኛ የሚባለውን መስዋዕትነት ከፍሎ ከቆርበቶው እሳት ውስጥ እንደወጣና መሪው አቢቹም በሕይወት እንደተረፈ ሰምተናል። ይኼን ጥያቄ ደጃዝማች የጠበቀው ጉዳይ ነው መሰለኝ፣ "መልክተኛ ልኬበታለሁ፣ ከዚህ ብዙ ሳይርቅ ሰፍሮ ከጀግኖቹ የትግል ጓዶቹ የከንባታ ልጆች ጋር እየተሰናበተ ነው" አለን። ደጃዝማች አበራ ለነአቢቹና ለከንባታ ልጆች መሰነባበቻ አንድ ሰንጋ፣ እንጀራና ጠጅ እንደላከ ወሬ ሰምተናል።

በማግሥቱ ሊነጋጋ ሲል ግድም ኮሎኔል ኮኖቫሎቭና አቶ ብረየር አሸለቡ። እኔና አበራ በረንዳ ላይ ቡሉኮዎቻችንን ተከናንበን በበርጩማዎች ላይ ተቀምጠን ስናወጋ፣ አንዲት የውሀ እንሥራ የተሸከመች ሴት በትንግርት እንሥራዋን እንደተሸከመች አንድ ቦታ ላይ ቆማ ለረጅም ጊዜ ፊዛ ወደምታይበት አቅጣጫ ተመለከትኩ። ምንም የሚታይ ነገር የለም። እኛ ካለንበት በጣም ብዙ ርቀው የሆኑ ፈረሰኛ የሚመስሉ ነገሮች ቆመዋል። ወዲያው ደጃዝማች ፈረሰኛ ወደሚመስሉት ነገሮች በጦር ሜዳ መነጽሩ አነጣጥሮ ጥቂት ከተመለተ በኋላ ሳቅ እያለ የጦር ሜዳ መነጽሩን እንዳይበት አቀበለኝ። እነዚያ ፈረሰኞች ወርቄ፣ አቢቹና ሀብቶም ነበሩ። "ለምን ወደዚህ አይመጡም?" ብዬ አበራን ጠየቅኹት። አሁንም እንደመሳቅ ብሎ፣ "አንበሳዋ ከራሶችም ሆነ ከሌሎች ጀሌዎቻቸው ጋር መገናኘት የፈለገች አልመሰለኝም፤ እስቲ ሌሎችንም እንቀስቅሳቸውና እነሱው ወደመረጡት ቦታ እንሂድ" አለና ወደ ውስጥ ገባ። እኛ ስንለባብስ አሽከሮች ፈረሶቻችንን ጭነውልን ስለነበር ጊዜ ሳናጠፋ እነአቢቹን ወዳየንበት ቦታ በፈረስ ሄድን። እነ አቢቹ ግን በቦታው አልነበሩም።

ብዙም ሳንቆይ ለጉዞ ተሰናድቶ የነበረው ከዚያ አስከፊ የቆርበቶ እልቂት የተረፈው ፈረሰኛው ጦር ጉዞ ሲጀምር አየነው። እግረኞቹ ወደኩዩ፣ ወደ አቦቴና ጃርሶ ከሄዱ ቆይተዋል፤ ከነዚህ ፈረሰኞች ሦስቱ የመንገድ መስመራቸውን ለውጠው እኛ ወደቀምንበት አቅጣጫ በዳለቻ፣ በግራጫና በጥቁር ፈረሶቻቸው ላይ ተቀምጠው ሽምጥ ሲጋልቡ አየናቸው። ጋላቢዎቹ ፈረሰኞች ግማሽ ርቀት ሲቀራቸው ፈረሶቻቸውን ገትተው ካቆሙ በኋላ፣ ጥቂት ሲነጋገሩ ቆይተው ባለጥቁሩ ፈረስ ፈረሰኛ ብቻውን ወደኛ መጋለብ ጀመረ። ባለጥቁሩ ፈረስ ጋላቢ ወደኛ እየተቃረበ ሲመጣ ማን እንደሆነ ሁላችንም ለየነው፤ የኛዋ ትንሿ ጀግና አቢቹ ናት።

ልክ እኛ የቆምንበት ቦታ ሲደርስ ፈረሱን ቀልምሞ እያሰቀመ ዱብ አለና ከደጃዝማች አበራ እግር ሥር ለጥ ብሎ ወድቆ ሰላምታውን ሊያቀርበ ሲል፣ ደጃዝማች አፈፍ አድርጎ አንሥቶ እንደታናሽ ወንድም፣ እንደጓደኛ እቅፍ አድርጎ ሳመው። በእቅፉ አስገብቶ ጀርባውን ቸብ ቸብ ካደረገ በኋላ ወደኛ ሲለቀው የደጃዝማች አበራ ዓይኖች እንባ አርግዘው ነበር። እናም ዞር ብሎ በሽማው አበሳቸው። ሁላችንም እያቀፍን ከሳምነው በኋላ በርቀት ወደሚጠብቁት ወንድሞቹ የሆነ ምልክት ከማሳየቱ ሁለቱ አንበሶች የትግል ጓዶቹና ወንድሞቹ እየጋለቡ ወደኛ ገሰገሱ። በዚህች የሰላሌ ሜዳ ላይ ንጹሕ አየር እየተነፈስን “አሁን ታዲያ ምን ታስባለህ? የትምህርት ነገር እንዴት ይታይሃል?” ብሎ ደጃዝማች ጠየቀው። አቢቹም ቆፍጠን ብሎ ሲመልስ፣ “ጠላት አገርን እየወረረ የምን ትምህርት ነው? በመጀመሪያ ኢትጵያ አገራችን ባለቤት ያላት መሆኗን ለጣልያን ማስተማር አለብን፤ እኔም የድርሻዬውን ለናት አገሬ አሠራለሁ” አለ። “ወዴት መሄድ አስበሃል? ብሎ ኮሎኔል ጠየቀው። “እንጃ ጌቶች፣ ምናልበት ጃርሶ ወደቆላው እንወርድ ይሆናል። ከከፋም ወደ ግንደበረት መዝለቃችን አይቀርም” አለ። አሁን ግን ትክዝ ብሎ “እማማን ሳታያቸው እንዳትወርድ፣ አደራ” አለው ደጃዝማች ትዕዛዝም ልመናም በተላበሰ ቃና።

አሁን አቢቹ እዝን ብሎ ቆይቶ፣ “ጌቶች፣ ትልቁ መከራዬም እሱ ነው፤ እንደምን ብዬ ዓይኗን አያለሁ። ሁለት ልጆቿን በተንቤን አንዱን ቀብሬ ሁለተኛውን ለጆቢራ ራት ጥዬ፣ እኔ ብቻ ተርፌ ፊቷ ስቀርብ ምን ትለኛለች?” አለ። “አይዞህ፣ የጀግኖች እናት ነችና ሁሉንም ትችለዋለች። ሂድና እያት። ብዙ ቀን ግን አትሰንብት። እኔም እንደነገሩ የቀረኝን ጦር አሰባስቤ ወደበረሀ መውረዴ አይቀርምና እንገናኛለን፤ ጥሩ ዋሻ ይዘህ ጠብቀኝ” አለ ደጃዝማች በማብራራት ዓይነት። ቀጠል አድርጎም ከኪሱ አንዲት የተጣጠፈች ወረቀት አውጥቶ “ለእማማ ስጣቸው” አለው። ለአቢቹ እናት ስለ ሁለቱ ልጆቻቸው አሟሟት የተጻፈ የማጽናኛ ደብዳቤ እንደሆነ ሁላችንም ገምተናል።

አቢ ደብዳቤውን በሁለት እጆቹ ጎንበስ ብሎ ተቀብሎ ወደ ኪሱ ከከተው በኋላ በመጀመሪያ ከወርቁ እጅ የተተጠቀለለውን ነገር ተቀብሎ ጨርቁን ከጣለ በኋላ አንድ ሽጉጥ ይዞ ለደጃዝማቹ፣ ለጦር አለቃው ስጦታ እያቀረበ፣ “ጌቶች፣ ከአንድ ከገደልኩት የጣልያን መኮንን እጅ ፈልቅቄ ያውጣሁት ነው። እነሆ ለማስታወሻ፣ ለወደፊት የነፃነት ትግላችንና ታማኝነታችን ይቀበሉኝ” ብሎ አቀርቅሮ ሽጉጡን የያዙትን ሁለት እጆቹን ለደጃዝማች ዘረጋቸው።

ደጃዝማች አበራ ሽጉጡን አገላብጦ ካየ በኋላ ፣ “አመስግናለሁ የኔ አንበሳ” ብሎ አቅፎ ሳመው። ቀጥሎ የሚያብረቀርቅ ስለታም ሰይፍ ይዞ “ኮሎኔል፣ ይኼ ደግሞ የወንድማችን የተሰፉ ጽዮን ሰይፍ ነው፤ እባክዎትን ለመከራ ጊዜ ማስታውሻ ይሆንዎት ዘንድ ይቀበሉኝ” ብሎ እንደ ኢትዮጵያውያን ወግ ሁሉ አንገቱን ሰብሮ ሰይፍ የያዙ እጆቹን ዘረጋ። ኮሎኔል እንባ እየተናነቀው ሰይፉን ተቀብሎ አቢቹን መተንፈስ እኪያቅታት ድረስ አቀፋት። ሌሎች ስጦታዎችን ሲያደርግ ከቆየ በኋላ የመጨረሻው ባለ ተራ እኔ ነበርኩና አሁን አቢቹ በእጁ ምንም ነገር ሳይዝ መጥቶ ከፊቴ ቆመ። ”ጌቶች፣ ለእርስዎ ምንም የምሰጠው ነገር የለኝም በማለት ትክዝ ብሎ፣ በተንቤን ሀ ብሎ የተዋጋባትን ሰይፉን መዝዞ እንድቀበለው

በሁለት እጆቹ ይዞ ለመነኝ። የገዛ ሰይፉን ለኔ መስጠቱ አግባብ እንዳልሆነ ለማስረዳት ብሞክርም አሻፈረኝ ስላለኝ ተቀብልኩት። አዎ አቢቹ ሌላ አንድ ሰይፍ አለው። በጣም የሚወደው፣ ወደ ጦር ሜዳ ሲሄድ አሻፈረኝ ብሎ የተከተለው፣ በመጀመሪያው ቀን ጦርነት በጀግንነት ሲዋጋ ወድቆ በዚያች ትንሽ ዋርካ ሥር የቀበረውና ለትልቁ ትግል ያደፋፈረው የወንድሙ ሰይፍ። የአቢ ሁለት ሰይፍ መታጠቅ ምሥጢር በዚህች ቅጽበት ተገለጠች። አቢቹ በመጨረሻ ከመሰነባበታችን በፊት ይህን ተናገረ።

> አባቶቻችን አያቶቻችን ይህችን አገር ዘር፤ ጎሣ እና ሃይማኖት ሳይመርጡ ሊወሩን የመጡትን ቱረኮች፤ ድርቡሾች ግብፆች፤ እንግሊዞችና ጣልያኖችን ተዋግተው ባያቆዩልን ኖሮ የዚህች አገር ባለቤት አንባልም ነበር፤ አሁንም በሞታችን እናቆያታለን፤ እኛ በሕይወት ባንገናኝ ልጆቻችን አገር ኖሯቸው በሰላም የሚፈነድቁባት እንደምትሆን አምናለሁ።

ከዚህች የአቢቹ አጭር የቃል ኪዳን ንግግር በኋላ ተቃቅፈን እንባ በእንባ እየተራጨን ያደረግናት ቆይታ የመጨረሻዋ የስንብት ሥነሥርዓት ነበረች።

የደራሲው ዘገባ ተፈጽሟል፤ የነ አቢቹ ታሪክ ግን እንደቀጠለ ይታመናል።

------------------/////--------------------